- 21 -

አንድ አማኝ ለችግርና መከራ የሚሠጠው ምላሽ

ዛሬ ላይ ያለው ሁኔታ ለሙስሊሙ አስቸጋሪ ነው። አንዳንዴ ተስፋ አለመቁረጥ በራሱ ከባድ ነገር ነው። ብዙዎቻችን ይህ ለምን ሆነብን ብለን እንገረማለን። ምንም ጥፋት ባላጠፋንበት ሁኔታ ይህ ነገር እንዴት ተከሠተ? እንላለን። ነፃነትንና ፍትህን መሠረታዊ ጉዳዮች ባደረጉ አገራት ጭምር በሙስሊሙ ላይ ማግለልና መድልዎ የሚደርሰው ለምንድነው? ውስጣችን የሚመላለሱ ጥያቄዎች ናቸው።

እነኚህ ሁሉ ሀሳቦች ትክክል ከመሆናቸው ጋር ከጀርባቸው ያሉ ነገሮችንም መመልከቱ ግድ ይላል። ከሚመስሉን ነገሮች ጀርባ ያለውን እውነታ ቆም ብለን እንመልከት። እውነታውን መመለከት ከፈለግን አይታችንን እንደገና ማሰተካከል ይኖርብናል።

እውነታው በቁርአን እና በሐዲሥ ውስጥ በተደጋጋሚ የተነገረ ትምህርት ነው። እውነታውም መሠረታዊ እውነት ነው። ምድራዊ ሕይወታችን በፈተና የተሞላች ናት። ሁሉም ነገር ለፈተና ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴾

> «ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መኾኑን ሊሞክራችሁ፣ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፣ እርሱም አሸናፊው መሃሪው ነው።» (አል-ሙልክ ፡ 2)

በዚህ መልኩ በግልፅ ተነግሮናል። አላህ ሕይወትንም ሆነ ሞትን የፈጠረው ለፈተና ነው። እኛን ለመፈተን ነው። ለቅጽበት አሰቲ የአደጋ ጊዜ ጠሩንባን/ጩኸት እናስተውል። ዓላማው ምንድነው? እሱ ሲጮህ የሚሰማን ነገር ምንድነው? ጩኸቱ አንድ መጥፎ ነገር የተከሠተ አሊያም ሊከሠት መሆኑን የሚያመላክት ነው። እሱን ስንሰማ እንዲሁ ወዲያው በደመነፍስ እንሸበራለን። ጩኸቱን እንዲሆን ያደረጉ አካላት ለሙከራ እያደረጉት ያለ ቢሆንስ? ምላሻችን ምን ሊሆን እንደሚችል እናስብ። ልምምድ እያደረጉ ቢሆንስ? የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ጩኸቱ (የልምምድ እና እውነተኛው) ያው ተመሳሳይ ናቸው። ግና ለፈተና የተደረገውም ቢሆን እውነት ይመስላል፣ ስሜት ይሠጣል፣ እውነት እንዲሰማን ያደርጋል። ግን አይደለም። ፈተና ብቻ ነው። በያንዳንዱ ፈተና/ሙከራ በተደጋጋሚ ይህንኑ እንድናስታውስ እንደረጋለን።

አላህ (ሱ.ወ.) ስለዚህ ምድራዊ ሕይወት እየነገረን ያለው ነገርም ይኸው ነው። ፈተናው የምር ይመስላል፣ ስሜት ይሠጣል፣ እጅግ እጅግ እውነታ ጋር ይመሳሰላል። ግና ለፈተና

ብቻ ነው። ፈተናውና ሙከራው በቦታችን ላይ ፀንተንና እጅግ ፀንተን እንድንቆም ከማድረግ ይልቅ አንዳንድ ጊዜ ያስነደነግጠናል፣ አንዳንዴ ያስጮኸናል፣ አንዳንዴ እንድንሸሽ ያደርገናል። ግና ፈተና መሆኑን አውቀን መረጋጋት ይኖርብናል።

ይህ ዓለም እና በውስጡ ያለው ሁሉ ፈተና ነው። ትክክለኛ ፈተና ግን አይደለም። ልክ እንደ የድንገተኛ አደጋ ጊዜው ጩኸት ነው ፈተናው። ትክክለኛ ለሆነው ነገር እያዘጋጀን ነው። ከጩኸቱ ጀርባ ላለው ነገር ሥልጠና እየሠጠን ነው።

የዚያ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ጩኸት ምንም ስሜት የማይሠጥ ነገር ባይሆን ምን ሊሆን ይችላል? እያንዳንዱ ቤት ያ ጩኸት እየመጣ ነው ተብሎ መልዕክት ቢደርሰውስ ?

በዚሁ መልኩ ከአላህ በኩል አስቀድሞ የሚደርሰንን መልዕክት እናጢነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፦

﴿ لَتُبْلَوُنَّ فِيٓ أَمْوَٰلِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ وَلَتَسْمَعُنَّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِكُمْ وَمِنَ ٱلَّذِينَ أَشْرَكُوٓا۟ أَذًى كَثِيرًا ۚ وَإِن تَصْبِرُوا۟ وَتَتَّقُوا۟ فَإِنَّ ذَٰلِكَ مِنْ عَزْمِ ٱلْأُمُورِ ﴾

«በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ በእርግጥ ትፈተናላችሁ። ከእነዚያም ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡትና ከእነዚያም ከአጋሩት ብዙውን ማሰቃየት ትሰማላችሁ። ብትታገሱና ብትጠነቀቁ ይህ ከጥብቅ ነገሮች ነው።»

(አሊ ዒምራን ፡ 186)

ከዚህ የማሳወቂያ መልዕክት በተጨማሪ ከዚህ ቀደም በዚሁ መልኩ ስለተፈተኑ በርካታ ማኅበረሰቦች እጅግ ብዙ መረጃ ተሠጥቶናል።

﴿ أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا۟ ٱلْجَنَّةَ وَلَمَّا يَأْتِكُم مَّثَلُ ٱلَّذِينَ خَلَوْا۟ مِن قَبْلِكُم ۖ مَّسَّتْهُمُ ٱلْبَأْسَآءُ وَٱلضَّرَّآءُ وَزُلْزِلُوا۟ حَتَّىٰ يَقُولَ ٱلرَّسُولُ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مَعَهُۥ مَتَىٰ نَصْرُ ٱللَّهِ ۗ أَلَآ إِنَّ نَصْرَ ٱللَّهِ قَرِيبٌ ﴾

«በእውነቱ የእነዚያ ከበፊታችሁ ያለፉት (ምእመናን መከራ) ብጤ ሳይመጣባችሁ ገነትን ልትገቡ ታስባላችሁን? መልክተኛውና እነዚያ ከርሱ ጋር ያመኑት "የአላህ እርዳታ መቼ ነው?" እስከሚሉ ድረስ መከራና ጉዳት ነካቻቸው፤ ተርበደበዱም። ንቁ! የአላህ እርዳታ በእርግጥ ቅርብ ነው (ተባሉም)።» (አል-በቀራህ ፡ 214)

የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ጩኸቱ አዲስ ነገር እንዳልሆነ እንዳልታሰበው ሁሉ ፈተናም አንደዚያው መለመድ አለበት።

ለምሳሌ የኛ ማኅበረሰብ ልዩ እንዳልሆን ተነግሮታል እንበል። ከዚያ ሁሉ ልምምድ በኋላ አንድ ጊዜ የጨኸቱ ድምፁን ከሰማን እንደ አዲስ ግብረመልስ አንሠጥም።የልምምድ እንኳን ቢደረግ መደናገጥ እና አለማመን ሊኖር አይችልም። እኛም አንሸበርም። ሌላዉ ቀርቶ ምንም የመጨነቅ ምልከትም አይታይብንም።

ግና ምላሽ እንሠጣለን።

ወሣኙ ነጥብም ያለው እዚሁ ላይ ነው። ለማነው ምላሽ የምንሠጠው? ማነው እየፈተነን ያለው? ማነው እያየ ያለው? የደህንነት ከፍሉ ወይስ ሌላ? የሳልናቸው ሁሉ ውሸት ናቸው። ባይሆን ሁሉም የፈተናው አካል ናቸው። ሁሉም ፈተናው የፈጠራቸው ናቸው እንጂ ምንም አይደሉም። እኛ ለአንድ እና አንድ ዳኛ ብቻ ነው ምላሻችንን የምንሠጠው። ለትክለኛው እና እውነት ለሆነው አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ። ምላሽ የምንሠጠው ከሱ አንፃር ነው። ምክንያቱም እሱ ነው እያየን ያለው። ለዚህ ፈተና ከምንሠጠው ምላሽ አንፃርም የሚገመግመንም እሱ ነው።

ይህን መሠረታዊ እውነታ እስከተገነዘብን ድረስ አንድ የሚያስገርም ነገር ይፈጠራል።ይህን ሀሳብ ወደ ውስጣችን ካስገባንና ከተላመድነው እሱ ፈተና ብቻ ነው የሚሆነው። ጥያቄያችንም በሚገርም ሁኔታ ይቀየራል። ከመጠየቅ ይልቅ ይህ ነገር እንዴት ሊከሠት ቻለ? ለምንድነው ሚዛናዊ ያልሆነው?... ከማለት ጥያቄያችን ይቀየርና ለዚህ ነገር በምን መልኩ ነው ምላሽ የምንሠጠው? እንዴት ነው ይህንን ፈተና የምናልፈው? ከዚህ ፈተና ምንድነው መማር የምችለው? በዚህ እውነት በሚመስል ነገር ውስጥ አልፌ እንዴት ነው አሻግሬ እየጎዳኝና እየጨቆነኝ ያለውን አካል መመልከት የምችለው? እንዴት ነው ፈተናውን ራሱ የማየው? እንደ አንድ ማኅበረሰብ ይህን ፈተና እንዴት ነው ወደ አላህ እንዲያቃርበኝ ላደርገው የምችለው? ይህን ፈተና ለተፈጠርኩበት ዓላማ እንዴት ላውለው የምችለው? ወደርሱ ለሚያቃርበኝ ነገር። አላሁ አክበር (አላህ ትልቅ ነው)!!

የአላህ ፈተና ውበቱና ልዩነቱ ከሳወቀን በኋላ መከሠቱ ነው። ከፈተናዎቹ አስቀድሞ ለፈተናዎቹ የሚያግዙንን ነገሮች ይልካል ትዕግስት፣ የአላህ ፍራቻ እና የመሣሉትን።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል :-

﴿وَمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَآ إِلَّا مَتَٰعُ ٱلْغُرُورِ ﴿١٨٥﴾ لَتُبْلَوُنَّ فِىٓ أَمْوَٰلِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ وَلَتَسْمَعُنَّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِكُمْ وَمِنَ ٱلَّذِينَ أَشْرَكُوٓا۟ أَذًى كَثِيرًا ۚ وَإِن تَصْبِرُوا۟ وَتَتَّقُوا۟ فَإِنَّ ذَٰلِكَ مِنْ عَزْمِ ٱلْأُمُورِ﴾

«ቅርቢቱም ሕይወት የመታለያ መሳርያ እንጅ ሌላ አይደለችም።

በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ በእርግጥ ትፈተናላችሁ። ከነዚያም ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡትና ከእነዚያም ከአጋሩት ብዙን ማሰቃየት ትሰማላችሁ። ብትታገሱና ብትጠነቀቁ ይህ ከጥብቅ ነገሮች ነው።»

(አሊ ዒምራን : 185-186)

በሌላ የቁርአን አንቀጽም ለሚደርስብን ችግር የተነሳ እንዳናመርር እና ብሶት እንዳናሰማ ሁለት ወሳኝ ነገሮችን ይጠቁመናል።

﴿ إِن تَمۡسَسۡكُمۡ حَسَنَةٞ تَسُؤۡهُمۡ وَإِن تُصِبۡكُمۡ سَيِّئَةٞ يَفۡرَحُواْ بِهَاۖ وَإِن تَصۡبِرُواْ وَتَتَّقُواْ لَا يَضُرُّكُمۡ كَيۡدُهُمۡ شَيۡـًٔاۗ إِنَّ ٱللَّهَ بِمَا يَعۡمَلُونَ مُحِيطٞ ﴾

«ደግ ነገር ብትነካችሁ ታስከፋቸዋለች። መጥፎም ነገር ብታገኛችሁ በርሷ ይደሰታሉ። ብትታገሱና ብትጠነቀቁም ተንኮላቸው ምንም አይጎዳችሁም። አላህ በሚሰሩት ሁሉ (በእውቀቱ) ከባቢ ነውና።» (ኣሊ ዒምራን : 120)

በዚህ ፈተና ማለፍ እንድንችል አላህ ሌላ መንገድም ይጠቁመናል። ከኛ በፊት የነበሩ ሕዝቦች ተፈትነው እንዴት እንዳለፉ...

﴿ ٱلَّذِينَ قَالَ لَهُمُ ٱلنَّاسُ إِنَّ ٱلنَّاسَ قَدۡ جَمَعُواْ لَكُمۡ فَٱخۡشَوۡهُمۡ فَزَادَهُمۡ إِيمَٰنٗا وَقَالُواْ حَسۡبُنَا ٱللَّهُ وَنِعۡمَ ٱلۡوَكِيلُ ١٧٣ فَٱنقَلَبُواْ بِنِعۡمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَفَضۡلٖ لَّمۡ يَمۡسَسۡهُمۡ سُوٓءٞ وَٱتَّبَعُواْ رِضۡوَٰنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ ذُو فَضۡلٍ عَظِيمٍ ١٧٤ إِنَّمَا ذَٰلِكُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ يُخَوِّفُ أَوۡلِيَآءَهُۥ فَلَا تَخَافُوهُمۡ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ﴾

«እነዚያ ሰዎች ለእነርሱ፦ ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው፤ ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው፥ በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ! ያሉ ናቸው። ከአላህም በኾነ ጸጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ። የአላህንም ውዴታ ተከተሉ፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው። ይሄችሁ ሰይጣን ብቻ ነው። ወዳጆቹን ያስፈራራችኋል። አትፍሩዋቸውም። ምእመናን እንደ ኾናችሁ ፍሩኝ።»

(አሊ ዒምራን : 173-175)

በሌላ የቁርአን አንቀጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይለናል፦

﴿ وَكَأَيِّن مِّن نَّبِيٖ قَٰتَلَ مَعَهُۥ رِبِّيُّونَ كَثِيرٞ فَمَا وَهَنُواْ لِمَآ أَصَابَهُمۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَمَا ضَعُفُواْ وَمَا ٱسۡتَكَانُواْۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٤٦ وَمَا كَانَ قَوۡلَهُمۡ إِلَّآ أَن قَالُواْ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَإِسۡرَافَنَا فِيٓ أَمۡرِنَا وَثَبِّتۡ أَقۡدَامَنَا وَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ١٤٧ فَـَٔاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ ثَوَابَ ٱلدُّنۡيَا وَحُسۡنَ ثَوَابِ ٱلۡأٓخِرَةِۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ

ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٤٨﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِن تُطِيعُوا۟ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ يَرُدُّوكُمْ عَلَىٰٓ أَعْقَٰبِكُمْ فَتَنقَلِبُوا۟ خَٰسِرِينَ ﴿١٤٩﴾ بَلِ ٱللَّهُ مَوْلَىٰكُمْ ۖ وَهُوَ خَيْرُ ٱلنَّٰصِرِينَ ﴾

«ከነቢይም ብዙ ሲታውንት ከርሱ ጋር ኾነው የተዋጉ ብዙ ናቸው። በአላህም መንገድ ለሚደርስባቸው ነገር አልፈሩም፤ አልደከሙምም። (ለጠላት) አልተዋረዱምም። አላህም ትእግስተኞችን ይወዳል። ንግግራቸውም "ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንንና በነገራችን ሁሉ ወሰን ማለፋችንን ለእኛ ማር፣ ይዞታችንንም አደላድል፣ በከሃዲዎችም ህዝቦች ላይ እርዳን" ማለታቸው እንጅ ሌላ አልነበረም። አላህም የቅርቢቱን ምንዳና የመጨረሻይቱን መልካም ምንዳ ሰጣቸው። አላህም በጎ አድራጊዎችን ይወዳል። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እነዚያን የካዱትን ሰዎች ብትታዘዙ ወደ ኋላችሁ ይመልሱዋችኋል። ከሳሪዎች ኾናችሁም ትገለበጣላችሁ።: (አይረዷችሁም)፤ ይልቁን አላህ ብቻ ረዳታችሁ ነው። እርሱም ከረዳቶች ሁሉ በላጭ ነው።» (አሊ ዒምራን: 146-150)

አላህ (ሱ.ወ.) እነኚህን ታሪኮች የሚነግረን ከታሪኮቹ ተምረን እኛም ጥሩ ለሆነ ምላሽ እንድንዘጋጅ ብሎ ነው። የነርሱ የቀደሙን ደጋግ ሰዎች ምላሽ የነበረው "ሐስቡነሏሁ ወኒዕመል ወኪል"/ "በቂያችንም አላህ ነው። ምን ያምርም መጠጊያ!" የሚል ነበር። የነርሱ ምላሽ እንደሚከተለው ነበር-

﴿ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَآ إِن نَّسِينَآ أَوْ أَخْطَأْنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَآ إِصْرًا كَمَا حَمَلْتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦ ۖ وَٱعْفُ عَنَّا وَٱغْفِرْ لَنَا وَٱرْحَمْنَآ ۚ أَنتَ مَوْلَىٰنَا فَٱنصُرْنَا عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴾

«ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፣ (አትቅጣን)። ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን። ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን። ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምሕረት አድርግ። አዘንልንም፣ ዋቢያችን አንተ ነህና። በከሓዲዎች ሕዝቦች ላይም እርዳን።» (አል-በቀራህ : 286)

የነርሱ ምላሽ የነበረው፤ ፈተናዎችንና መከራዎችን ዘወር ብሎ አለመመልከት ነው። እውነት ከሚመስሉ ነገሮች ባሻገር ተመልከቱና እውነታውን አዩ። እውነታው አላህ (ሱ.ወ.) ነበር። ፈተናው ከአላህ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ከፈተና የሚያድነውም አላህ ብቻ መሆኑን አወቁ። ስለሆነም ወደ አላህ በመመለስ፣ በትዕግስት እና በመልካም ባህሪና እና አሱን በመጠንቀቅ የሱን እገዛ ፈለጉ። ከሁሉም በላይ ዋስትና የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) አማኞችን ያረጋጋበትና በስኬትም ለነርሱ ቃል የገባበት ሁኔታ ነበር። እንዲህ በማለት፦

﴿ وَلَا تَهِنُوا۟ وَلَا تَحْزَنُوا۟ وَأَنتُمُ ٱلْأَعْلَوْنَ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿١٣٩﴾ إِن يَمْسَسْكُمْ قَرْحٌ فَقَدْ مَسَّ ٱلْقَوْمَ قَرْحٌ مِّثْلُهُۥ ۚ وَتِلْكَ ٱلْأَيَّامُ نُدَاوِلُهَا بَيْنَ ٱلنَّاسِ ۚ وَلِيَعْلَمَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَيَتَّخِذَ مِنكُمْ شُهَدَآءَ ۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٤٠﴾ وَلِيُمَحِّصَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَيَمْحَقَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٤١﴾ أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا۟ ٱلْجَنَّةَ وَلَمَّا يَعْلَمِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ جَٰهَدُوا۟ مِنكُمْ وَيَعْلَمَ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴾

«እናንተም የበላዮች ስትሆኑ ምዕመናን እንደኾናችሁ አትስነፉ፣ አትዘኑም። ቁስል ቢያገኛችሁ ሰዎቹንም መሰሉ ቁስል አግኝቷቸዋል። ደኽችንም ቀናት በሰዎች መካከል እናዘዋውራታል። (እንድትገሰጹና) አላህም እነዚያን ያመኑትን እንዲያውቅ (እንዲለይ) ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው። አላህም በደዮችን አይወድም። አላህም እነዚያን ያመኑትን (ከኀጢአት) ሲያነጣና ከሃዲዎችን ሲያጠፋ ነው። በእውነቱ አላህ ከናንተ እነዚያን የታገሱትን ሳያውቅ (ሳይለይ) ታጋሾቹንም ሳያውቅ ገነት ልትገቡ አሰባችሁን»

(አሊዒምራን ፡ 139-142)

ሕይወታችንን የምንመለከትበትን መነጽር አንዴ መቀየር ከቻልን፤ ለነገሮች የምንሠጠው ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ምላሻችን በሚገርም ሁኔታ ይቀየራል። ከኛ በፊት የነበሩ ደጋግ ሰዎች ሲፈተኑ የጨመረላቸው ነገር ቢኖር በጽናት ላይ ጽናት በእምነት ላይ እምነትን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ይህንኑ ይነግረናል። አንድ ጊዜ የሆነውን እንዲህ በማውሳት ፡-

﴿ وَلَمَّا رَءَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلْأَحْزَابَ قَالُوا۟ هَٰذَا مَا وَعَدَنَا ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَصَدَقَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ ۖ وَمَا زَادَهُمْ إِلَّآ إِيمَٰنًا وَتَسْلِيمًا ﴾

«አማኞቹም አህዛብን ባዩ ጊዜ፣ ይህ አላህና መልእክተኛው የቀጠሩን ነው፤ አላህና መልእክተኛውም እውነትን ተናገሩ፤ አሉ። (ይህ) እምነትና መታዘዝንም እንጂ ሌላን አልጨመረላቸውም።» (አል- አሕዛብ ፡ 22)

ግና የማያ መነጽራችንን እስካልቀየርን ድረስ ወደፊት መንቀሳቀስ አንችልም። አሻግረን መመልከትም አንችልም። “ይህ ነገር በኛ ላይ እንዴት ሊከሠት ቻለ?” ለሚለው ምላሽ ለማግኘት መጀመርያ የፈተናውን ዓላማ ራሱን መጀመርያ ያስፈልጋል። እኛን ለማጥራት፣ ለማጠንከር እንዲሁም እኛን ሁላችንንም ጠላቶቻችንን ጭምር ወደ ፈጣሪያችን ለማቅረብ የተፈጠሩ ናቸው።